# አውደ ኢትዮጵያ

ሰኔ 15 2008

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው!

እትም 28


## ብርቱካንም ሌሎቹም እስረኞቹ ይፈቱ!!!

## አቶ መለስ - ዉሸቱ ይብቃና ብርቱካንን ይፍቱ !

የሕወሃት/ኢሕአዴጉ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ሃርድቶክ ለተሰኘዉ ታዋቂ የቢቢሲ ፕርሮግራም ላይ ቃለ-መጠይቅ መስጠታቸዉ በሰፊዉ ተዘግቧል። በርካታ ጉዳዮች በቃለ መጠይቁ ላይ የተነሱ ሲሆን፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ዙሪያ አቶ መለስ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ግን እርስ በርሱ የሚቃረን፣ እራሳቸዉንና ድርጅታቸዉ ያስገመተና በደጋፊዎቹ አፍሪካን ወክሎ በጂ-20 ስብሰባ ላይ ቀረበ ከተባለ መሪ የማይጠበቅ ነበር።

በአንጻሩም ደግሞ በዚህ ቃለ መጠይቅ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ምን ያህል የአለም አቀፉን ሜዲያ የሳቡ ታላቅ መሪ መሆናቸዉን የታየበት ቃለ መጠይቅ ነበር።

የቢቢሲዋ ዛይናብ ባዳዊ «የአንድነት ለዲሞክራስና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ብርቱካን ሚደቅሳ ለእድሜ ልክ እሥር ቤት ናት። አምንስቲ ኢንተርናሽናል እንዲሁም ሌሎች፣ ወ/ት ብርቱካን ለመታሰራቸዉና ለመያዛቸዉ ምንም አይነት ሕጋዊ ምክንያት የለም ይላሉ» በማለት የወት ብርቱካን መታሰር አለም አቀፍ ተቃዉሞን እንዳስነሳ ከገለጹ በኋላ «ለምን ታሰረች ?» ሲሉ ጥያቂያቸዉን ለአቶ መለስ አቀረቡ።

አቶ መለስ ገለልተኛና አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ላይ ያላቸዉን ንዴት ከፊታቸዉ እያሳዩ «ትክክለኛ የፍርድ ቤት ዉሳኔ ሌላ ምን አይነት ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ይፈልጋሉ?» ሲሉ በአለም አቀር የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ላይ ያላቸዉን ቅሬታ ገልጸዉ፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰነዉ ዉሳኔ ፍጹም ትክክለኛና ፍትሃዊ የሕገ ሂደት እንደተከተለ በመግለጽ ምላሽ ይሰጣሉ።

የቢቢሲዋ ወ/ሮ ዛይናብ ባዳዊ፣ የአቶ መለስ ዜናዊ መልስ አልተዋጠላትም። «ምን አደረገች ? በ 1997 ፣ ከምርጫዉ በኋላ፣ ምርጫዉ ተጭበርብሯል አለች። በዚያ ምክንያት ለሁለት አመት ገዳማ ታሰረች። እንደገና ተለቀቀች። አሁን ደግሞ እራሷን እንደገና እሥር ቤት አገኘቻዉ።» ሲሉ በወት ብርቱካን ሚድቅሳ ላይ የተወሰደዉ እርማጃ ሕጋዊ ነብር የሚለዉ ክርክር እንዳላሳመናቸዉ ገለጹ።

አቶ መለስ ዜናዊ በወ/ት በርቱካን ላይ የተወሰደዉን እርምጃና ወደዚያ ያደረሰዉን ሂደት ሲገልጹ፡ «ሕገ መንግስታዊ ያልሆነ የመንግስት ለዉጥ ለማምጣት በተደረገ እንቅስቃሴ ዉስጥ በመካፈሏ ተከሰሰች። ነጻና ገለልተኛ በሆነ ፣ ከአዉሮፓ ማሕበር የመጡ ተወካዮች በታዘቡት የፍርድ ችሎቱ ጉዳይዋ ታይቶ ተጠናቀቀ። ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ናት ብሎ ወሰነ። የእድሜ ልክ እሥራት ፈረደባት። ከዚያ በኋላ ይቅርታ ጠየቀች። እኛም ይቅርታ ሰጠናት። ተለቀቀች። ከተለቀቀች በኋላ ይቅርታ እንዳልጠየቀች ተናገረች።» በማለት ነበር ለማስረዳት የሞከሩት።

ከዚህ በፊት ወንጀል ሰርተዉ ምህረት የተደረገላቸዉ ሰዎች ሌላ ወንጀል ሲሰሩ ዳግመኛ ሊታሰሩ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። ነገር ግን በየትም አገር ምህረት ተሰጥቶ ፣ ምህረቱ ከተሰጠ ደግሞ ከአመት በላይ ሆኖ፣ ሌላ ተፍጸመ የተባለ ወንጀል ሳይኖር፣ ያለፈዉን መልሶ በመምዘዝ፣ ከዚህ በፊት ምህረት በተሰጠበት ጥፋት ተመልሶ ሰዎችን ያሰረ መንግስት ታይቶም ተሰምቶም

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሰሌፍ በዋይት ሃዉስ ዋሽንግተን ዲሲ (አባይ ሚዲያ ፎቶ)

## በአለም ዙሪያ የዲሞክራሲ ድምጻ እያስተጋባ ነዉ !

ከአራት አመት በፊት ነበር፣ በ 25 ሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጹን ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሰጠዉ። ግንቦት ሰባት ቀን 1997 ዓ.ም። ያኔ፣ ደርግ ከወደቀ ጀመሮ ሲነገረዉና ሲያደነቁረዉ የነበረዉን የዘር ፖለቲካ አልፈልግም ብሎ፣ ሕዝቡ ለኢትዮጵያዊነት ድምጹን የሰጠበት ቀን ነበር። ያኔ ሌሊት ተነስቶ ወደ ምርጫ ጣብያ በመሄድና ለሰዓታት በመሰለፍ የዲሞክራሲያዊ መብቱን ሕዝቡ ያረጋገጠበት ቀን ነበር።

በዚያን ቀን በማያሻማ መልኩ ኢትዮጵያዊዉ ድምጹን ቢሰጥም ጉልበተኞች ግን በጠመንጃ ኃይል ድምጹን ሰርቀዉ፣ ኮሮጆ ለወጠዉ፣ ሰላምዊዜጎችን በጥይት ገድለዉ፣ በአሥር ሺህ የሚቆጠሩትን በግፍ አስረዉ .. በስልጣን ላይ ተቀምጠዋል። ይህ ሁሉ ሆኖም ግን በህዝብ ዉስጥ በግንቦት ሰባት 1997 ሰሞን የተለኮሰዉ የነጻነትና የዲሞክራሲን ንቅናቄ ግን አልተገታም።

በሌላ በኩል ይህን ንቅናቄ ለማፈን ሕወሃት/ኢሕአዴግ፣ ያለ የሌለ ኃያሉን በመጠቀም በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያደርገዉን ጥረትም ቀጥሏል።

በዚህም ምክንያት እንደ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አንጋፋ የፖለቲካ መሪዎችንና እንደ ቴዲ አፍሮ አይነት የሰላምና የፍቅር መልእክተኞች በግፍ እያሰረ፣ የተቃዋሚ ሰላማዊ ታጋዮችን እያዋካበ ፍጹም አምባገነናዊነትን እያሳየ ነዉ።

በዉጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንም የኢትዮጵያ ህዝብ አካል እንደመሆናቸዉ በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ቴዲ አፍሮና ሌሎች የሕሊና እሥረኞች እንዲፈቱ ድምጻቸዉን እያሰሙ ናቸዉ።

ሜያዚያ 27 ቀን 2001 ዓ.ም በአውስትራሊያ በምትገኝ የፐርት ከተማ፣ እንዲሁም ግንቦት 2 ቀን

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ሰልፍ በሎንደን (አባይ ሚዲያ ፎቶ)

## አንብበው ለወገን ያስተላልፉ

# አገር ወዳድነቷንና ሰላማዊነቷን በተግባር አሳይታለች። እኛስ ?

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በቃሊቲ እሥር ቤት በጨለማ ክፍል ዉስጥ በግፍና በጭካኔ እንድትቀመጥ ከተደረገ 140 ቀናት አልፏታል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ገዢዉ ፓርቲ ያስረበት፣ «ይቅርታ መጠየቋን ካደች» የሚለዉ ምክንያት ፍጹም ዉሸት የተሞላበት፣ ሕገ ወጥና አምባገነናዊ እንደሆነ በሰፊዉ ተዘግቧል።



ገዢዉ ፓርቲ የ«የይቅርታዉ» ነገር አሳስቦታ ወይንም ለሕግ የበላይነት ተቆርቁሮ ሳይሆን፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የምትመራዉ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሕጋዊነትን ባገኘ በአጭር ጊዜ ዉስጥ እጅግ ትልቅ ተስፍ ሰጪ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ በማቻሉና፣ በሚመጣዉ የ2002 ምርጫ ከሥልጣናችን ሊያስወግደን ይችላል በሚል ስጋት እንደሆነ የማያጠራጥር ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ከማሰር በተጨማሪ፣ ገዢዉ ፓርቲ ሌሎች የአንድነት ፓርቲን ለማዳከም የወሰዳቸዉ ዘርፈ ብዙ ጸረ-ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎችም አሉ።

በቅርቡ በመገናኛ ብዙሃን በሰፊዉ እንደተዘገበዉ «መንግስት የመገልበጥ ሙከራ አድርጋቿል» በሚል፣ ሁለት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ላዕላይ ምክር ቤት አመራር አባላት ክስ ቀርቦባቸዋል። እነዚህም ሁለት ጠንካራና አንጋፋ የድርጅቱ አመራር አባላት፣ በሰሜን ኢትዮጵያ የአንድነት ፓርቲ ዋና አስተባባሪ አቶ መላኩ ተፈራና የወጣቶች አስተባባሪ አቶ አቢዩ በለዉ ናቸዉ።

አቶ አቢዮ በለዉ በገዢው ፓርቲ የደህንነት አባላት ቤታቸዉ እንደተከበበ ሲያወቁ በድብቅ ከአገር ለቀዉ ለመሰደድ በቅተዋል። አቶ መላኩ ተፈራ ደግሞ፣ ምንም ባላጠፉት ጥፋት፣ በሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ እንደሆነ እየታወቀ፣ በሽብር ሥራ ተከሰዉ ወህኒ ወርደዋል።

ለቀበሌ፣ ለወረዳ፣ ለዞንና ለክልል ባለሥልጣናት ስዉር መመሪያ በመስጠት ገዢዉ ፓርቲ የአንድነት ፓርቲ በየክፍለ አገራቱ የሚያደርጋቸዉን እንቅስቃሴዎች ለመገደብ ትልቅ ሙከራ እያደረገም ነዉ። አንዳንድ ጽ/ቤቶ እንዲዘጉ እየተደረገ ሲሆን፣ የክልል አመራራ አባላትም ከፍተኛ እንግልት እየደረሰባቸዉ ነዉ።

ይህ በአቶ አቢዩ በለዉና በቶ መላኩ ተፈራ ላይ ያነጣጠረዉ ጥቃት፣ እንዲሁም በየክልሉ ያሉ አባላት ላይ የሚደርሰዉ ወከባ ያለምንም ማጋነን የአንድነት ፓርቲን ለማዳከም ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ እንደሆነ ነዉ በግልጽ የሚያሳየን።

ሌላዉ ገዢዉ ፓርቲ በአንድነት ፓርቲ ላይ እያደረገ ያለዉ ጫና በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ፣ በሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሃን በኩል

## ርዕሰ አንቀጽ

የሚያሰራጨዉ ርካሽ የፖሮፖጋንዳ ዘመቻዎች ናቸዉ።

የአንድነት ፓርቲ ልዩነቶችን የሚያከብር፣ በዉስጡ ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ለማለማመድ የሚሞክር፣ በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚያምን ፓርቲ እንደመሆኑ አለመስማማቶች፣ የሃሳብ ግጭቶች በፓርቲ ዉስጥ መኖራቸዉ የግድ ነዉ። አመራራ አባላቱም ላይ በየጊዜዉ ተቃዉሞዎች ይቀርባሉ።

የሃሳብ ግጭትና ክርክር የሌለበት፣ መሪዎችም ተጠያቂ የማይሆኑበት ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ፣ በፍጹም አምባገነንነት የተተበተበ፣ ሚስጥራዊ በሆነ አሰራር የሚንቀሳቀስ እንደ ሕወሃት/ኢሕአዴግ አይነት ፓርቲ ነዉ።

ታዲያ የአንድነትን ዲሞክራሲያዊ ባህሪ የፈጠረዉን ዲሞክራሲያዊ የሃሳብ ክርክሮችን በማጣመም፣ ድርጅቱ እየተከፋፈለ እንደሆነ ለማሳየትና በሕዝብ ያለዉን አመኔታ ለመጉዳት፣ እንደ ኢትዮ ቻናልና አይጋ ፎረም የመሳሰሉ አፍቃሪ ኢሕአዴግ ጋዜጦችና ድህረ ገጾች የዕለት ተዕለት ሥራቸዉን ሆኗል።




ሰልፍ በተባበሩት መንግስታት ቢሮ ጄኔቫ (አባይ ሚዲያ ፎቶ)

እንግዲህ ገዢዉ ፓርቲ ያለ የሌለ ኃያሉን ተጠቅሞ ለሕዝብ ተስፋ ይሆናል የተባለዉንና የቅንጅት ወራሽ ነኝ የሚለዉን ፓርቲ የማዳከም ሥራዉን ሲሰራ፣ በአንጻሩ የአንድነት ደጋፊዎች የበለጠ ቀበቷችንን ታጥቀን ለትግሉ የሚያስፈልገዉን መስዋእትነት ለመክፈል መዘጋጀት ያለብን ወቅት ነዉ። ትግሉ እየመረረ ሲመጣ ወደ ኋላ የምንልበትና ተስፋ የምንቆርጥበት ጊዜ አይደለም።

የአንድነት ፓርቲ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ከጅምሩ ሲንቀሳቀስ የከፋ ችግር ሊመጣ እንደሚችል እያወቀ ነዉ። መሪዎቹ ደግሞ ሊታሰሩ እንደሚችሉ እያወቁ ነዉ። ስለዚህ ትግል አልጋ በአልጋ ስላይደለ፣ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ሊያጠፋዉ እየሞከረ ያለዉን የዲሞክራሲያዊ ሰላማዊ እንቅስቃሴ የምናቀጣጥልበት ጊዜ ነዉ።

የአንድነት ፓርቲ የአመራር አባላትም በአንድ በኩል የታሰሩትን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳናን አቶ መላኩ ተፈራን እንዲሁም ሌሎች የድርጅቱ አባላትን ለማስፈታት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በየክልሉ የሚያደርጋቸዉን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ማፋፋም ይጠበቅባቸዋል። የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት፣ በዚህ በከፋ ወቅት፣ ጥቃቶች ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየተወረወሩ እንደሆነ ተረድተዉ፣ በጥበብና በማስተዋል፣ በታላቅ ትህትና ትግሉን የሚመሩ፣ ህዝብን ከኋላ አሰልፈዉ የሚጓዙ፣ ብርቱካን ሚደቅሳ ትመራዉ የነበረ እንቅስቃሴና ትግል፣ በብርቱክን መታሰር እንዲዳከም ሳይሆን፣ እንደዉም ብርቱካን በመታሰሩ የበለጠ ትግሉ እንዲጠናከር የሚያደርጉ መሆን አለባቸዉ እንላለን። ለዚህም ይህን ታላቅና አገራዊ ሃላፊነታቸዉን ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከጎናቸዉ እንደምንቆምም ቃል እንገባለን።

ኔልሰን ማንዴላና ዋልተር ሲሱሉ ሲታሰሩ እነ ዊኒ ማንዴላ ትግሉን በደቡብ አፍሪካ ያጧጧፉት እንደነበር፣ አሁን በኢትዮጵያ ትግሉ መጧጧፍ አለበት እንላለን። በጨዋታዉ መሃል ተስፋ ከቆረጥን፣ የጀመርነዉን ጉዞ መጨረስ ካቃተን፣ መሪዎቻችን ዋጋ የከፈሉበትን ችቦ አንስተን ካልተጓዝን፣ የሰላምዊ ትግል አይሰራም ብለን ሜዳዉን ለሕወሃት/ኢሕአዴግ ብቻ ከለቀቅን፣ ትግሉን ከኢትዮጵያ አዉጥተን ወደ ባዕድ አገር ካደረግን፣ የኢትዮጵያን ትንሳዔ በቶሎ እንደማይመጣ መገንዘብ አለብን እንላለን።

ጊዜዉ በጣም ወሳኝ ጊዜ ነዉ። እጆቻችን አጣጥፈን የምንቀመጥበት፣ ከንፈራችንን የምንመጥበት፣ እርስ በርስ የምንወቃቀስበትና ተስፋ የምንቆርጥበት ጊዜ አይደለም። ጊዜዉ ጥርሳችንን ነክሰን፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ በጥቃቅን ልዩነቶች እርስ በርሳችን መጋጨታችንን አቁመን፣ ማንም የማይበግረዉን ሕዝባዊ፣ ሰላምዊ ንቅናቄን የምናነሳሳበት ጊዜ ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ «እኛ ዝግጁ ነን። እናንተ ዝግጁ ናችሁ» ብላ ጠይቃ ነበር። እርሷ ዝግጁነቷን አሳይታለች። ለእዉነት፣ ለፍትህ፣ ለሰላም፣ ለዲሞርካሲና ለአገራችን አንድነት ጠመንጃ ሳትይዝ አምባገነኖቻችን ገጥማለች። ሀቀኝነቷንና ቆራጥነቷን፣ አገር ወዳድነቷንና ሰላማዊነቷንና በተግባር አሳይታለች። እኛስ ?



የሰልፍ መሪዎች ከተ.መንግስት የሰው መብት ድርጅት መሪዎች ጋር ሲነጋገሩ

# ሶስት ትውልድ አይለቅ ተነሱ እንነሳ!!!

## ከትንሳኤ ለአገር

እያሸማቀቀ ቅስም እየሰበረ ተስፋ እያስቆረጠ፣
እያነካከሰ ሞራል እየነካ ቂም እያስቋጠረ እያበላለጠ፤
ትውልድ የሚያጠፋ የክፋት ፍሬ ነው በእሾህ የተዋጠ።
አሰቃይቶ ገዳይ መርዘኛ ነው እርሱ የአገርም ነቀርሳ፣
ህሊና የሌለው ለራሱ እማያስብ ያነሰ ከእንስሳ።

እስቲ እዩት እናንተ!
በመጦርያ ዘመን በድካም በእርጅና፣
የእስር ቤት ደጃፍ ላይ ሲሉ ጎንበስ ቀና።
እነ እግዜር አይፈሬ እነ አገር ጠላቱ ሲፈጥሩ ወከባ፣
ይህን ሳላይ በሞትኩ እያሉ ሲያለቅሱ ሊኮሩ ሲገባ።
የቤት መሪ ሆነው ሲሉ ሽቅብ ቁልቁል፣
ማጣፊያው ሲያጥራቸው ጉልበታቸው ሲዝል።
እንባ ሽቅብ ረጭተው ለሰማይ ለእግዜሩ፣
አገር እህል እንጂ ጀግና አይራባት አሉ ለመኑ ተጣሩ።

ሁለተኛው ትውልድ ጎልማሳ ወጣቱ የአገሩ ምሰሶ፣
ወይ ስደት ይገፋል ወይም ወደ እስር ቤት ተለቅምና ታፍሶ።
መናገር እንዳይችል ማሰብ እንዲጠፋው ግራ እየተጋባ፣
አሳር ያሳዩታል አፍነው ለጉመው ያጨናንቁታል በነጋ
በጠባ።
ስራም እንዲጠፋው ከእውቀትም እንዲርቅ ራሱን እንዲጠላ፣
ቅጥረኛቸው እንዲሆን ተስፋ እየቆረጠ በችጋር ሲቆላ፤
በሀሰት ምላሳቸው እየሸነቆጡ በዘር ትንተናቸው እየዘላበዱ፤
እጅ ይሰጣል ብለው አገቱት አሰሩት ሰብዕናውን ካዱ።
በክፋት መጥረቢያ እየቸረቸፉ በጥላቻ መጋዝ እየገዘገዙት፣
ሁለተኛው ትውልድ የአገሩን ምሰሶ እንደ ምስጥ በሉት።
እንዲህ እንደዋዛ ዘመናት ከነፉ ጠፋለት አምሳያ፣
ፊት የነበረ አገር ሁዋላ እየተሳበ ሆነን መሳለቂያ።

እዩት ሶስተኛውን
ጨቅላ እምቦቃቅላ በልቶ ያልጠገበ ዘልሎ ያላማረበት፣
ቡዝዝ ቅዝዝ ያለ አያቱ ሀዘንተኛ ወላጁ ከእስር ቤት።
ፍቅር እየጠማው መጠየቅን ፈርቶ ጓጉቶ ተቁለጭልጮ፣
ተስፋ እየጨለመው ሳቅም እየራበው ኮስምኖ ቀጭጮ።
ልጅነቱን ነጥቀው ተስፋውን መንጭቀው ከጡት እያስጣሉ፣
ሶስተኛውን ትውልድ እንዲህ ያቆስላሉ እንዲህ ይገድላሉ።

በዘመናት ብዛት በብልሀት በዘዴ አድብተው ሊያጠፉ፣
በእውቀት አቀጭጨው የሕጻናትን ተስፋ ህይወት የሚቀጥፉ፤
ደካማ አረጋውያንን እረፍት እየነሱ በእንባ ይሚያራጩ፣
ወጣት ጎልማሳውን በዘር በሀይማኖቱ በጾታ እሚያጋጩ።
ራሳቸውን እንኳ በተድላ በምቾት እያንደላቀቁ፣
መኖር ያልቻሉበት በስጋት በፍርሀት የሚሸማቀቁ።
የሳጥናዔል ልጆች የክፋት ሰራዊት የአገርም ነቀርሳ፣
ህሊና የሌለቸው ማሰብ በማይችሉ ያነሱ ከእንስሳ።
ሶስት ትውልድ አይለቅ ተነሱ እንነሳ!!!
አገር አትበተን ተነሱ እንነሳ!!!

የሶስት ትውልድ ምሳሌ የሆኑኝ ወ/ሮ አልማዝ ፣ ወ/ት ብርትኳንና ሕፃን ሃሌ ናቸው። የሁላችንም ቤት በዚህ ምሳሌ ውስጥ አለ። ጧሪ የሌለው አረጋዊ ሞቱን ይመኛል፣ ሀገርም ያለ ተረካቢ ትውልድ ወና ነች። ያለጦር የምትፈታ ያለ ጠበቃ የምትረታ ባዶ መሬት!!! አገሩን ለባዕድ ልጆቹን ለባርነት ለመሸጥ የሚፈቅድ ምን አይነት ኅሊና ያለው ይሆን???



ብርቱካን ትፈታ !



በርን ሲዊዘርላንድ





ሮም ኢ.ታሊ



በርሊን ጀርመኒ




# በአለም ዙሪያ...

ከገጽ 1 የዞረ

2001 በለንደን ከተማ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳንና ሌሎች የሕሊና እሥረኞችን በማስታወስ የሻማ ማብራት ሥነሥርዓት ተከናዉኗል። በነዚሁ ሥነ ሥርዓቶች ኢትዮጵያዉያኑ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዲገነባና ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳንና ሌሎች የሕሊና እሥረኞቸ እንዲፈቱ ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርጉ በመግለጽ ነበረ የትግሉ ሙሉ አጋርነታቸዉን የገለጹት።

«መሪያችን ወ/ት ብርቱካን ትፈታ ፣ ቴዲ አፍሮ ይፈታ፣ የሕሊና እሥረኞች ይፈቱ » የሚሉና ሌሎች መፈክሮችን በማንገብ ፣ ግንቦት 2 ቀን 2001 ድምጻቸዉን በሰልፍ ያሰሙት ደግሞ በአትላንታ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ነበሩ። የኢትዮጵያ ሴቶች ሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ተወካይ ወ/ሮ ፊፊ ደርሶ ለሰልፈኛዉ ባደረጉት ንግግር፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር በጣም መቆጣታቸዉን ገልጸዉ፣ ገዢው ፓርቲ እያደረገ ያለዉን አፈና በማወገዝ፣ ወ/ት ብርቱካንን ለማስፈታት ድርጅታቸዉ አሁን የሚያደርገዉን ጥረት በእጥፍ እንደሚጨምር ገልጸዋል።

የማህደር አንድነት ሬዲዮ ተወካይ አቶ ደረጄ ዘወዴ፣ የኢሕአፓ ዲሞክራሲያዊ ተወካይ አቶ ተስፋሁን ገብረ ሚካኤልና የአትላንታ አንድነት ድጋፍ ማህበር ሊቀመንበር አቶ ግርማይ ግዛዉ ንግግር ያደረጉ ሲሆን፣ ድርጅቶቻቸዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳንና ሌሎች የሕሊና እሥረኞች እስኪፈቱና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እስኪሰፍን ድረስ ለአንድ አፍታ እንደማይተኙ አረጋግጠዋል።

አትላንታ ሰልፍ በተደረገ በአምስት ቀኑ፣ በግንቦት ሰባት ቀን 2001 ዓ.ም፣ የአለም ቀፍ ሰልፍ አስተባባሪ በጠራዉ አለም አቀፍ ሰልፍ በስዊዘርላንድ በጄኔቫና በበርን፣ በለንደን፣ በስቶክሆልም፣ በበርሊን ጀርመን፣ በኦስሎ ኖርዌይ፣ በሮም ጣሊያንና በዋሺንግተን ዲሲ ኢትዮጵያዉያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች፣ የአረንጓዴ ቢጫ ቀን ባንዲራን እያወለበለቡ፣ በትልቁ የተዘጋጀ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳንና ቴዲ አፍሮን ፎቶ አንግበዉ፣ ድምጻቸዉን ሲያሰሙ ዉለዋል። ሰልፈኞቹ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች የሕሊና እሥረኞች በአስቸኳይ እንዲለቀቁ የጠየቁ ሲሆን አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉን አገዛዝንም የሚያወግዙ መፈክሮችን አሰምተዋል።

ይህ ሰላማዊ ሰልፍ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከታሰሩ ቀን ጀምሮ ቢቆጠር፣ አራተኛዉ ታላቅ ሰላምዊ ሰልፍ ሲሆን፣ በተከታታይ ሰልፎ እንዲህ መደረጋቸዉ የሚያሳየዉ አንድ ቁልፍ ጉዳይ ቢኖር፣ በኢትዮጵያዉያኑ ዘንድ ያለዉን ትልቅ ቁርጠኝነት ነዉ። ወያኔ/ኢሕአዴግ እንደ ብርቱካን ሚደቅሳ አይነት ታላላቅ መሪዎችን አስሮ መቀመጥ እንደማይችል ኢትዮጵያዉያኑ በድጋሚ ያረጋገጡበትም ቀን ነበር።

በሚቀጥለዉ እትም በሰፊዉ የግንቦት ሰባትን ሰልፉ ዝርዝር ዘገባ ይዘን እንደምንቀርብ በትህትና እየገለጥን፣ ሳይታክቱ በጣም አስደሳች ሥራ ለሰሩት የሰልፉ አስታባባሪዎች ያለንን አድናቆትና ምስጋና በዚህ አጋጣሚ እንገልጻለን። በርቱ፣ ተበራቱም እንላለን።

**ኢትዮጵያን እናድናት፣ እንጠብቃት!! እግዚአብሄር አእምሮና ጉልበት ቸሮናል ተግባር ግን ከኛ ይጠብቃል!!**

# አቶ መለስ - ዉሸቱ...

ከገጽ 1 የዞረ

አይታወቅም። ህወሃት/ኢሕአዴግ በወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ላይ ያደረገዉ የመጀመሪያዉ ሳይሆን እንደማይቀር ነዉ።

ወ/ሮ ዛይናብ በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም በመገረም «እና እሥር ቤት እንደገና መለሳቹሃት ?» በማለት ጠንከር ባሉ ቃላት የጠየቀችዉ። አቶ መለስ ዜናዊ «ይቅርታ አልጠየኩም ካለች፣ ይቅርታ የተሰጣት ደግሞ ይቅርታ ሳትጠይቅ በተሳሳተ መንገድ ነበር ማለት ነዉ። ያ ከሆነ ደግሞ በሕጋችን መሰረት በተሳሳተ መንገድ ይቅርታ ሳይጠየቅ የተሰጠ ምህረት ወዲያዉኑ መሰረዝ አለበት።» በማለት ለወሰዱት አሳፋሪና ሕገ ወጥ የጭካኔ እርምጃ፣ ሊጨበጥ የማትል፣ ከአንድ የአይምሮ ሕመምተኛ የሚቀርብ አይነት የተምታታበት መልስ በመመለስ በምንም አይነት መጸጸት እንደሌለባቸዉ ያሳዩት።

አቶ መለስ ዜናዉ በዚህች አጭር መልሳቸዉ በርካታ ከእዉነት የራቁና እርሳቸዉን ግምት ዉስጥ ያስገባቸዉ የተሳሳታ አባባሎችን ጠቅሰዋል።

- በቅንጅት መሪዎች፣ በሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችና በጋዜጠኞች ላይ የቀረበዉን ክስ ያዳመጠዉና በነርሱም ላይ የፍርድ ዉሳኔ የሰጠዉን ፍርድ ቤት ነጻና ገለልተኛ ነበር ሲሉ ነበር አቶ መለስ የተናገሩት። እንደሚታወቀዉ የቀድሞ የቃሊት እሥረኞች ያንን ፍርድ ቤት ገለልተኛ ነዉ ብለዉ እዉቅና አልሰጡትም። በዚህም ምክንያት ጉዳያቸዉን በዚያ ፍርድ ቤት አላቀረቡም። ስለዚህ አንድ ተከሳሽ እራሱን መመከት ባልቻለበት ሁኔታ የሚደረግ የፍርድ ሂደት ነጻና ገለልተኛ ነበር ማለት አይቻልም።

  ያ ብቻ አይደለም አቶ መለስ ዜናዊ የፍርድ ሂደቱ ከአዉሮፓ የመጡ ታዛቢዎች እንደታዘቡትም ገልጸዋል። እርግጥ ነዉ በእንግሊዛዊዉ የሰብዓዊ መብት ጠበቃ፣ ማይክል ኤልማን፣ የሚመራ የታዛቢዎች ቡድን ነበር። የታዛቢ ቡድን ባቀረበዉ ሪፖርት ግን የፍርድ ቤቱ ሂደት የአለም አቀፍ መስፈርትን ያላሟላ፣ ፍጹም ገለልተኝነት የማይታይበት ጨዋታ እንደሆነ ነበር የገለጸዉ። በዚህም ምክንያት አቶ መለስ ዘናዊ እራሳቸዉ፣ በፈረንጆች አቆጣጠር ኦክቶበር 2006 ዓ.ም፣ የታዛቢዉ ቡድን ያቀረበዉን ሪፖርት በመቃወም፣ ከአዉሮፓ ማህበረሰብ አምባሳደሮችና ከአዉሮፓ ሕብረት ተጠሪ ቲመቲ ክላርክ ጋር ባደረጉት ስብሰባ በሪፖርቱ ላይ ያላቸዉን ተቃዉሞ ማሳወቃቸዉ ይታወቃል።
- አቶ መለስ ዜናዊ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጥፋተኛ ከተባለች በኋላ ይቅርታ እንደጠየቀች ነዉ ይገለጹት። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ቃሌ» በሚለዉ ጽሑፋቸው የነበሩትን ክስተቶች በግልጽና በዝርዝር ለመጀመሪያ ጊዜ አቅርበዉታል።

  ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳና ሌሎች የቀድሞ የቃሊቲ እሥረኞች በሕሊናቸዉ ምንም ወንጀል እንደሌለባቸዉ ያታወቃሉ። እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ንጹህ አይምሮ ያለዉና ነገሮችን በሚገባ ማገናዛብ የሚችል ማንኛዉም ሰው፣ ጥፋት እንደሌለባቸዉ ያዉቃል። ነገር ግን የነበረዉን የፖለቲካ ቀውስ ለመፍታት፣ በአገራችን ከፍ የሚያስፈልገዉ የእርቅና የሰላም መንፈስ እንዲወርድ፣ አሥራ ስምንት ወር የፈጀ የአገር ሽማግሌዎች ጥረት በኋላና ለገገረዉ ፓርቲ የመዉጫ በር ለመክፈት ሲባል የኢትዮጵያ ህዝብንና መንግስትን ይቅርታ ጠይቀናል ብለዉ ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ፈረሙ። በሽማግሌዎቹና በአቶ መለስ ዜናዊ ቃል የተገባዉ የነበረዉ የፍርድ ሂደቱ እንደሚቋረጥ ነበር። ነገር ግን በሽምግሌዎቹም ሆነ በአቶ መለስ ዜናዊ የተገባዉ ቃል አልተጠበቀም።

  አቶ መለስ ዜናዊ፣ የቃሊቲ እሥረኞችን ፊርማ በእጃቸዉ ካስገቡ በኋላ የፍርድ ሂደቱን ከማቋረጥ ይልቅ ፍርድ ቤቱ ቶሎ ቶሎ በመቀመጥ የእድሜ ልክ እሥራት በችኮላ እንዲበየንባቸዉ ተደረገ።

  እዚህ ላይ እንደምናየዉ አቶ መለስ ዜናዊ እንዳሉት፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጥፋተኛ ከተባሉ በኋላ አይደለም ይቅርታ የጠየቁት። ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ናችሁ ብሎ ከመወሰኑ ከሳምንታት በፊት፣ ለእርቅና ለሰላም ሲሉና የአገር ሽምግልና ወግን በማክበር ብቻ ነበር ይቅርታ የጠየቁት። በሌላ አባባል የተገኘዉ ይቅርታ ሕጋዊ ይቅርታ ሳይሆን በአገር ባህልና ወግ መሰረት የተደረገ ይቅርታ ነበር።

  ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የቀድሞ የቃሊቲ እሥረኞችም በዚህ መንገድ እንደተፈቱ ነዉ የተናገሩት። የአገር ሽማግሌዎች ያኔ እሥረኞች በተፈቱ ጊዜ በግልጽና በገሃድ የገለጹትም የቃሊቲ እሥረኞች ሊፈቱ የቻሉት በእነርሱ በአገር ሽምጋሌዎች ጥረት እንደሆነ ነበር።
- አቶ መለስ ዜናዊ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ይቅርታ አልጠየኩም» ብላለች ሲሉም ከሰዋል። ይሄም ፍጹም የተሳሳተና ከእዉነት የራቀ የዉሸት አባባል ነዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ «ቃሌ» በሚለዉ ታሪካዊ ጽሁፏ እንዳቀረበችዉ የኢትዮጵያ ህዝብንና መንግስትን ይቅርታ መጠይቋን አልካደችም። በግልጽ የነበረዉን ሁኔታ አስቀምጣለች።

  ደግሞ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳም ሆነ ሌሎች ይቅርታ ጠይቀዉ ይቅርታ አልጠየቅንም ቢሉም እንኳን፣ መንግስት ከልክ ያለፈ አረመኒያዊ ድርጊት ላይ የሚሰማራበት ምክንያት አንዳች አልነበረም። ከዚህ በፊት የተፈረመዉን ወረቀት በማሳየት ወ/ት ብርቱካን ይቅርታ ሆነ ሌሎች ይቅርታ እንደጠየቁ ማሳወቅ ይበቃ ነበር።

አቶ መለስ ዜናዊ ሆኑም ጓደኞቻቸዉ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የወሰዱት እርምጃ በፍጹም የተሳሳተና እንደ ጨዋ ሊከራከሩበት የማይችሉበት ጉዳይ እንደሆነ እነርሱ የሚያጡት አይመስለንም። የሚመልሱት መልስ አያጡም የሚባሉትና በደጋፊዎቻቸው የሚደነቁት አቶ መለስ ዜናዊ እራሳቸዉ፣ በዚህ በቢቢስ ሃርድቶክ ቃለ መጠይቅ ሲደናበሩ ነዉ ያየነዉ። ጋዜጠኛ ዛይናብ ባዳዊ ይሄን ጊዜ በዉስጧ በጣም እንደታዘበቻቸዉ በማከታተል ከጠየቀቻቸዉ ጥያቄ መገመት ይቻላል።

አሁንም ሕወሃት/ኢ.ሕአዴግ በብርቱካን ሚደቅሳ ዙሪያ በየጊዜዉ ጣያቄዎች ይቀርብለታል። የወ/ት ብርቱካን ጉዳይ ባላሥልጣናቱ በሄዱበት ቦታ ሁሉ እንደጥላ ይከተላቸዋል። እዉነት፣ ሀቁ ፣ ከወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ጎን ስለሆነ በምንም አይነት ሁኔታ በጭፍን የሚከተሏቸዉን ካድሬዎች ካልሆነ በቀር ማገናዘብ የሚችሉና ትንሽ ትምህርት የገባቸዉን ሌሎች ሰዎች ለማሳመን አይችሉም። በምንም ሚዛን ሕጋዊና ሰላምዊ እንቅስቃሴን የምታደርግ፣ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሕግ እዉቅና የተሰጠዉ ሰላማዊ የፖለቲካ መሪ ፣ ያወም ይቅርታ መጠየቋን ሳትክድ፣ ይቅርታ አልጠየኩም ብላላች ተብሎ ማሰር፣ የሚያስኬድና ተቀባይነት ያለዉ ድርጊት አይደለም።

በመሆኑም ገገረዉ ፓርቲ ለራሱ ሲል ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በአስቸኳይ መፍታት አለበት እንላለን። አቶ መለስ ዜናዊ ዉሸቱ ይብቃና ብርቱካንን ይፈቱ እንላለን። እዉነት ከብርቱካን ጋር ነዉ። ህዝብ ከብርቱካን ጋር ነዉ። የአለም አቀፉ ማህበረሰብና የአለም አቀፉ ሚዲያ ከብርቱካን ጋር ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን እሥር ቤት በቆየች ቁጥር ገገረው ፓርቲ የበለጠ እየተጎዳ ነዉ የሚመጣዉ። የፖለቲካ አየሩ የበለጠ እየደፈረሰ አገራችን ወደ ከፋ ሁኔታ እያመራች ነዉ የምትመጣዉ።

ምናልባት የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን መታሰር የአንድነት ፓርቲን ለማዳከም ይረዳናል፣ ወደፊት የሚደረገዉን የ2002 ምርጫ በቀላሉ ማሸነፍ እንችላለን በሚል ጭፍን ስሜት ከሆነ የገገረዉ ፓርቲ አመራር አባላት አሁን እያደረጉት ያለዉን ጨካኝ ተግባራት የሚያደርጉት፣ አስተዋይ መካሪ ቢፈልጉ ይሻላል እንላለን። ይህ ድርጊታቸው የበለጠ በነርሱ ላይ የነበረዉን ተቃዉሞ የሚያጠናክር እንጂ የሚያዳፍን አይደለም።

**አትላንታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴንቨር * ሎሳንጀለስ* ላስቬገስ * ሚኒያፖልስ * ናሽቪል * ኦክላንድ * ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ * አፐ ሰቴኢት ኒኦርክ * ዋሽንግተን ሜትሮ**

**ለአንድነት ለዲሞክራሲ ለፍትህ ፓርቲ ( ቅንጅት) በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መሀበር**
1334 9th Street, NW. Suite # 1 Washington DC. 20001***ስልክ (202)** 462 0556
**ፋክስ: (202)** 462 0557.***ኢ.ሜል:** Email: info@andinetusa.org
**http://www.andinetusa.org**

**አስተያየቶን በ** awdethiopia@gmail.com **ይጻፉልን**